**ETHIOPIAN HERITAGE**

**SOCIETY IN NORTH AMERICA**

**የኢትዮጵያ ውርስና ቅርስ ማኅበር በሰሜን አሜሪካ**

1317 Orren Street NE, Washington, DC 20002

president@ehsna.org

pr@ehsna.org

703-718-6809

---

መስከረም 9 ቀን 2013 ዓ.ም.

(September 19, 2020)

ጉዳዩ፤ <u>ኢትዮጵያ ውስጥ እየተፈጸመ ስላለው ጀኖሳይድና የንብረት ውድመት አፋጣኝ መፍትሔ እንዲፈለግለት ስለማሳሰብ</u>

የኢትዮጵያ ውርስና ቅርስ ማኅበር በሰሜን አሜሪካ (ኢ.ው.ቅ.ማ.ሰ.አ.) ጥር 2003 ዓ.ም. ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የቀደሙ አባቶቻችንና እናቶቻችን ያወረሱንን ታሪክ፣ ትውፊትና ቅርስ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍና ተተኪው ትውልድ በአገራችን ባሕልና ወግ እንዲታነጽ በማድረግ በኩል ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷና አንድነቷ የተጠበቀ እንዲሁም ዜጎቿ በሰላም የሚኖሩባት አገር እንድትሆን የኢ.ው.ቅ.ማ.ሰ.አ. ጽኑ ምኞት አለው። ድርጅቱ ከኢትዮጵያ አኩሪ ታሪክ ውስጥ ግምባር ቀደም የሆነውን የአድዋ ድል በማስመልከት የታሪክ ምሁራንን፣ ተመራማሪዎችንና ታዋቂ ግለሰቦችን በመጋበዝ ለረዥም ዓመታት ውጤታማ ዝግጅቶችን አካሂዷል። ከዚህም በተጨማሪ በሜሪላንድ ክፍለ ሀገር ውስጥ በሚገኘው የሞንትጎመሪ አውራጃ ውስጥ የአድዋ ድል በአዋጅ እንዲዘከርና እንዲታሰብ አስደርጓል።

ድርጅታችን እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ተቋም የህዝብን ሰላምና ደህንነት የሚመለከቱ ጉዳዮችን ይከታተላል። በዚህም መሠረት ካለፉት ሁለት ዓመታት ተኩል አንስቶ በተለየ ሁኔታ በበርካታ የአገሪቷ ክፍሎች ውስጥ እየደረሰ ያለው ማንነትንና ሐይማኖትን መሠረት ያደረገ ጥቃት በእጅጉ አሳዝኖናል አስቆጥቶናልም። የተሳሳተ የፖለቲካ አስተሳሰብ የወለደው የጭካኔ ድርጊት የዜጎች ፍጅትን፣ ንብረት ውድመትን፣ ዘረፋን፣ የአብያተ ክርስትያናትን መቃጠል በማስከተሉ በእጅጉ አሳዝኖናል፣ አስቆጥቶናልም። ክርስቲያንና ሙስሊም ተከባብሮና ተፋቅሮ በሚኖርባት አገር ውስጥ በማናቸውም ቤተ እምነት ላይ የሚደርስ ጥቃት እጅግ ከባድ ወንጀል በመሆኑ በዝምታ መታለፍ እንደሌለበት እናምናለን።

ኢትዮጵያዊያን በፈለጉትና በመረጡት ቦታ የመኖርና የመሥራት ህጋዊ መብታቸው ተጥሶ ለስደተኞች ሊደረግላቸው የሚገባ ሰብዓዊ እንክብካቤ እንኳ ተነፍጓቸው፤ አያት ቅድመ አያቶቻቸው ተወልደው ባደጉበትና እትብታቸው በተቀበረበት ቦታ እጅግ በሚሰቀጥጥ ሁኔታ አማራና የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ተከታይ በመሆናቸው ብቻ ተለይተው ሲታረዱና አካላቸው ሲቆራረጥ፣ አይናቸው ተጎልጉሎ ሲወጣ፣ እርጉዝ ሴቶች ማህጸናቸው በጩቤ ተዘርግፎ ጽንሳቸው ሲጨነግፍና አስከሬናቸው ተቆራርጦ ሲጣል ከመመልከት የከፋ መከራ በዚህ ዓለም ላይ ይመጣል ብሎ ማሰብ አይቻልም። ይህ ታይቶም ተሰምቶም የማያውቅ ዘግናኝ ድርጊት አገራችን ውስጥ በመፈዘሙ ከልብ አዝነናል።

ይህ ሁሉ ጭፍጨፋና ውድመት ሲካሄድ የመንግሥት አካላት የሆኑት መከላከያ ሠራዊት፣ ፖሊሶችና "ልዩ ኃይሎች" እንዲሁም የአስተዳደር ሠራተኞች፣ እልቂቱን ማስቆምና የዜጎችን ህይወት መታደግ ሲገባቸው የጥፋቱ ተባባሪ ሆነው መገኘታቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎች ተለቀዋል። የአማራ ብሔረሰብ አባላትና የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና ተከታዮች ስም ዝርዝርና የሚኖሩበት የቤት ቁጥር ተለይቶ ቤታቸው ውስጥ እያሉ በመንግስት እይታ ሥር እንዲጨፈጨፉ ተደርገዋል። ግድያው የተፈጸመው ቤታቸው ውስጥ መሆኑ ግድያው በዕቅድ የተመራና የአካባቢው ሹመኞች እጅ እንዳለበት የሚያረጋግጥ ነው። በተግባር ከደረሰው አኳያ በጥቂቱ ጠቀስነው እንጅ ዘርና ሐይማኖት ላይ ያተኮረ እጅግ የሚዘገንና የሚሰቀጥጥ የጭካኔና የጥላቻ ድርጊት ተፈጽሟል።

በኢትዮጵያ የወንጀለኞች መቅጫ ሕግና በዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድንጋጌዎች መሠረት እየደረሰ ላላው የዘር ማጥፋት (ጀኖሳይድ) አፋጣኝ መፍትሔ እንዲፈለግለት እንጠይቃለን። መንግሥት ከፈለገ ሮጦ የመድረስ አቅሙ እንደ አውሎ ነፋስ ፈጣን መሆኑን በሶማሌ ክልል፣ በአማራ ክልልና በቅርቡም በዎላይታ ዞን ከተወሰዱት እርምጃዎች ለመረዳት ይቻላል።

ሆኖም በቡራዩ፣ በሻሸመኔ፣ ኮፈሌ፣ ዝዋይ፣ በባሌ፣ዶዶላ፣ሀረር፣ድሬዳዋ፣ መተከልና ሌሎችም ቦታዎች ይህ ፍጥነት አለመታየቱ ያሳዝናል። ይዋል ይደር ሊባል የማይገባውና አሁኑኑ ሥራ ላይ መዋል ያለበት ኦሮሚያና ሌሎች ክልሎች ውስጥ በአማራዎችና በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተከታዮች ላይ ጀኖሳይድ የሚፈጽመውን እጅግ አነስተኛ ቁጥር ያለውን ወንጀለኛ የቄሮ መንጋ በቁጥጥር ስር አውሎ ለፍርድ ማቅረብ ነው። **የዘር ማጥፋት** (ጀኖሳይድ) የማስቆምና ወንጀለኞችን ለፍርድ የማቅረብ እንዲሁም የአገሪቷን ሰላምና ደህንነት የማስጠበቅ ኃላፊነትን መንግሥት በአፋጣኝ እንዲወጣ እያሳሰብን፤ የኢትዮጵያ ውርስና ቅርስ ማህበር እንደ አንድ ተቆርቋሪና ጉዳዩ እንደሚመለከተው ተቋም ከዚህ በታች የሚከተሉትን ማሳሰቢያዎች ያቀርባል፤

1. የወንጀል ድርጊትን መደበቅ የህዝብን አመኔታ ስለሚያጠፋ ቡራዩ፣ ሻሸመኔ፣ ኮፈሌ፣ ዝዋይ፣ ባሌ፣ዶዶላ፣ ሀረር፣ ድሬዳዋ፣ መተከልና ሌሎችም ቦታዎች  ውስጥ የተፈጸመው ተራ ወንጀል ሳይሆን **<u>የዘር ማጥፋት (ጀኖሳይድ)</u>** ስለሆነ በትክክለኛው የወንጀሉ ስም ጀኖሳይድ ወይም የዘር ማጥፋት ተብሎ እንዲገለጽ እንጠይቃለን።

2. በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገራት በሚገኙ በዜና ማሰራጫዎችና በማህበራዊ መገናኛዎች ላይ የጥላቻና *"የግደለውና የእረደው"* አዋጅ አውጀው፣ የጥቂት ወጣቶችን አዕምሮ በጥላቻ መርዘው ጀኖሳይድ ያደረሱ ቡድኖች፣ ግለሰቦች፣ ድጋፍ ሰጪዎችና እንዲሁም ሆን ብለው የጥፋቱን ሀሳብ ያፈለቁና የተባበሯቸው የመንግሥት አካላት ሁሉ ማንነታቸው ተጣርቶ ለፍርድ ማቅረብ የመንግስት ኃላፊነትና የስራ ድርሻ መሆኑን ለማስገንዘብ እንወዳለን።

3. የቤተሰብ አባላት ለተገደሉባቸውና ለተፈናቀሉ ወገኖች እንዲሁም ቤታቸው፣ ሱቃቸው፣ መኪናቸው፣ መጋዘናቸውና ልዩ ልዩ ዓይነት ንብረቶቻቸው ለወደመባቸውና ለተዘረፋባቸው ዜጎች በአስቸኳይ ካሳ የመስጠትና ሕይወታቸው እንደገና እንዲቀጥል የማድረግ ኃላፊነት የመንግሥት መሆኑን ለማስገንዘብ እንወዳለን።

4. በተደራጀ የመንጋ ጥቃት የፈረሱ ሃውልቶች ተመልሰው የነበሩበት ቦታ ላይ እንዲተከሉ አንዲሁም የተቃጠሉና የፈረሱ ቤተክርስቲያኖች፣ መስጊዶችና ሌሎችም የማህበረተሰብ መገልገያዎች ተመልሰው እንዲገነቡ እየጠየቅን በዚህም የመልሶ መገንባት ሥራ ድርጅታችንም ሆነ ሕዝብ ተሳታፊ እንዲሆን እድሉ እንዲመቻች እንጠይቃለን።

5. ቤተክርስቲያኖች፣ መስጊዶች፣ ሀውልቶች፣ ቅርሶችና የተለያዩ የማሕበረሰብ ንብረቶች ላይ ጥቃትና ዝርፊያ እንዳይደርስ መንግሥት ልዩ ጥበቃ እንዲያደርግ እየጠየቅን ሕዝቡም ቅርሶችንና የማሕበረሰብ መገልገያዎን በመጠበቅና በመንከባከብ ረገድ ከመንግሥት ጋር ተባብሮ መስራት እንዳለበት እናሳስባለን። እኛም ለዚህ ተግባር የበኩላችንን አስተዋጽኦ ለማበርከት ዝግጁ መሆናችንን እንገልጻለን።

6. ከሁሉም በላይ ለዚህ ሁሉ ጥፋት ምንጭ የሆነውን የውሸት የታሪክ ትርክትና በቅጥፈት የተበከለ የፖለቲካ መስመርን ማምከን በተመለከተ መንግሥት ሳያሰልስ ለሁሉም ዜጎች የሚሰጥ የሰውን ልጅ ክብርና የአብሮነትን ጥቅም የሚያስገነዝብ አገር አቀፍ ሰፊ የተሀድሶ ዘመቻ እንዲያደረግ አጠንክረን እንጠይቃለን። መሠረተ ቢስ በሆነ የሀሰት የታሪክ አስተሳሰብና የጥላቻ ፍልስፍና ላይ ተመርዞ ያደገ ወጣት ከማጥፋት አይድንምና አስተሳሰቡን ለማስተካከል መንግስትና ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል የሥራ ድርሻና ኃላፊነት መሆኑን እየጠቆምን እኛም አቅማችን በሚፈቅደው መጠን ለመተባበር ዝግጁ መሆናችንን አንገልጻለን።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይጠብቅ!

የኢትዮጵያ ውርስና ቅርስ ማሕበር በሰሜን አሜሪካ

ግልባጭ፤

ለኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት

ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት

ለኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት

ለኢትዮጵያ ባሕል ሚኒስቴር

ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ጉባዔ

ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር (ስቴት ዲፓርትመንት)

አፍሪካ ዋች

ጀኖሳይድ ዋች

የአውሮፓ ኮሚሽን

ኢንተርናሽናል ክራይሲስ ግሩፕ

ለአምነሲት ኢንተርናሽናል

ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ (WCC)

ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን

ለኢትዮጵያ ኤምባሲ፣ ዋሽንግተን ዲሲ